# VOTE EARLY BY ABSENTEE BALLOT

VOTE 2025

*በሚኖሶታ እስከ ዋናው የምርጫ ቀን ድረስ መጠበቅ የለቦትም- ከዛ በፊት፡ በኣካል ተገኝተው ለማይመርጡና ከምርጫው ቀን በፊት ለሚመርጡ በምሰጥ የምርጫ ወረቀት በግዜ ምረጡ!*

## በኣካል ተገኝተው ከቀኑ በፊት ምረጡ

ከዋናው የምርጫ ቀን 46 ቀናት በፊት፡ በዕለቱ ዕለት፡ በኣካል ተገኝተው ለማይመርጡ ሰዎች የሚሰጥ የምርጫ ወረቀት በመጠቀም ሊመርጡ ይችላሉ። ሰዓትና ቦታ ለማወቅ mnvotes.org ጎብኙ።

## ቀደም ብለው በፖስታ በመላክ በግዜ ምረጡ

በኣካል ተገኝተው ለመምረጥ ለማይችሉና ለማይፈልጉ እንዲሁም ከቀኑ በፊት ለመምረጥ ለሚፈልጉ የሚሰጥ የምርጫ ወረቀት በፖስታ እንዲላክልዎ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ።

① mnvotes.govን በመጎብኘት በማንኛውም የዓመቱ ግዜ የምርጫ ወረቀት ለማግኘት ኣመልከቱ። የኣስመራጭ ኮሚቴ ባለስልጣኖች፡ የምርጫ ወረቀቶቹ ከተዘጋጁ ይልኩሎታል። (ቀናቱን ለማወቅ በስተጀርባ ይመልከቱ)

② ከምርጫ ወረቀትዎ ጋር የሚመጡትን መመርያዎች በደንብ ኣድርገው ይመልከቱ። የሚሞላውን ሁሉ ካልሞሉ፡ ምርጫዎ ኣይቆጠርም።

③ ሲመርጡና የምርጫ ወረቀትዎን ሲያጠናቅቁ የዓይን ምስክር ያስፈልጎታል። ይህ ምስክር የተመዘገበ የሚኖሶታ መራጭ ወይም ህጋዊነት ያለው መስርያ ቤት ወኪል ሊሆን ይችላል። ምስክሮ የሲግኔቸር ፖስታው ላይ መፈርምና ኣድራሻውን ማስፈር ኣለበት።

④ ለመምረጥ ካልተመዘገቡ፡ በሚላክልዎ ወረቀት ውስጥ የምዝገባ ማመልከቻ ፎርም ያገኛሉ።

ከበስተጀርባ ይቀጥላል...

### የ2025 ቀናት

የማጣርያ ምርጫ
ማክሰኞ፡ ነሃሴ 12 ቀን

በኣካል ሳይገኙ የሚደረግ ምርጫ
በፖስታ መምረጥ ወይም በኣካል ተገኝተው የሚመረጥበት ቀን - ከመስከረም 19ቀን እስከ ህዳር 3 ቀን

ለመምረጥ ተመዝገቡ
በዋናው ምርጫ ቀን፡ ግዜ ለመቆጠብ ቀደም ብለው በግዜ እስከ ጥቅምት 14 ቀን ለመምረጥ ይመዝገቡ።

የምርጫ ቀን
ማክሰኞ ህዳር 4 ቀን

*የሚኖሶታ የኣገር ውስጥ ኣስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት*

*mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE*

# VOTE EARLY BY ABSENTEE BALLOT

VOTE 2025

*...ከበፊቱ ገጽ የቀጠለ*

ለመመዝገብ ያስፈልጋሉ ተብለው ከተዘረዘሩት የመታወቅያ ኣማራጮች ውስጥ ኣንዱን ለዓይን ምስክሮ ያሳዩ። የዓይን ምስክሮ ከመታወቅያ ወረቀቶች ኣማራጮች ውስጥ የትኛውን እንዳሳዩት በሲግኔቸር ፖስታ ውስጥ ምልክት ማድረግ ኣለበት።

⑤ ከጨረሱ በውሃላ የምርጫ ወረቀቱንና ፎርሙን ወድያውኑ ይላኩ። የምርጫ ወረቀትዎ ከዋናው የምርጫ ቀን <u>በውሃላ</u> ከደረሰ <u>ኣይቆጠርም</u>። የምርጫ ወረቀትዎን ወደ ላከሎ የምርጫ ጣብያ በኣካል ሂደው መስጠትም ይችላሉ።

## *የምርጫ ወረቀትዎ ምን ላይ እንደደረሰ ተከታተሉ*

በፖስታ የተላኩ ወይም በኣካል የተሰጡ የምርጫ ወረቀቶችና በትክክል የተሞሉ ፎርሞች በግዜ ከደረሱ ይቆጠራሉ። mnvotes.govን በመጎብኘት የምርጫ ወረቀትዎ ምን ላይ እንደደረሰም ሆነ በግዜ መድረሱንና መቆጠሩን ለማረጋገጥ ይችላሉ።

| *የ2025ቀናት* | **የማጣራት ምርጫ** | **ኣጠቃላይ ምርጫ** |
|---|---|---|
| **የምርጫ ወረቀቶች መላክ የሚጀመርበት ቀን** | ዓርብ ሰኔ 27 | ዓርብ መስከረም 19 |
| **በፊት ቢያመለክቱ ይመረጣል** | ዓርብ ሓምሌ 11 | ዓርብ ጥቅምት 3 |
| **የምርጫ ወረቀት የሚቀበሉበት የመጨረሻ ቀን** | የምርጫ ቀን ማክሰኞ ነሃሴ 12 | የምርጫ ቀን ማክሰኞ ህዳር 4 |

*የሚኖሶታ የኣገር ውስጥ ኣስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት*

*mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE*